## የመድኃኒቱ ውጤታማነት

ሚሶፕሮስቶልን ከተጠቀሙ ከ10 ሴቶች ውስጥ ለ9ኙ እርግዝናን ለማቋረጥ ይሰራል።

## መድሃኒቱ ካልሰራ የምናደርገው፡-

የሚሶፕሮስቶልን መጠን በመድገም ወይም በመሳሪያ የታገዘ ፅንስ የማቋረጥ ሂደት (Manual Vacuum Aspiration) በመጠቀም ፅንሱን ማቋረጥ።

ሚሶፕሮስቶልን ከወሰዱ በኋላ እርግዝናው የሚቀጥል ከሆነ በሚወለደው ህፃን ላይ ትንሽ የጤና እክል ይገጥማል።

## ፅንስ የማቋረጥ ሂደቴ የተሳካ ይሆን?

አንዲት ሴት እርጉዝ እንዳልሆነች ከተሰማት ፅንስ የማቋረጥ ሂደቱ የተሳካ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። በህክምና ፅንሱን ካቋረጠችበት ጊዜ አንስቶ ከ 3 እስከ 4 ሳምንታት ባለው ጊዜ ውስጥ የእርግዝና ምርመራ ወይም የአልትራሳውንድ ምርመራ ማድረግ አለባት።

**ልብ ይበሉ፡-** ምናልባት ሴቲቱ ካልደማች፣ ትንሽ የደም መፍሰስ ካለ (ከወር አበባ ያነሰ እና ያልረጋ ደም ከሆነ) እና ወይም የመድሀኒት እንክብሎቹን ከተጠቀመች በኋላ የእርግዝና ምልክቶች ከታዩባት አሁንም እርጉዝ ልትሆን ትችላለች። እርግዝናው እንደቀጠለ ወይም እንደተቋረጠ ለማረጋገጥ በተቻለ ፍጥነት የአልትራሳውንድ ምርመራ ማድረግ አለባት። ይህ የማይቻል ከሆነ ደግሞ እንደገና እንክብሎቹን መጠቀም ትችላለች።

## ፅንሱ ከተቋረጠ በኋላ

አንዲት ሴት ፅንሱ ከተቋረጠ በኋላ ከ 1 እስከ 3 ሳምንታት ቀላል የደም መፍሰስ ሊያጋጥማት ይችላል ነገር ግን እያንዳንዱ ሴት ላይ የተለያየ ሊሆን ይችላል። ከዚህ በኋላም ፅንስ የማቋረጥ ሂደቱ የተሳካ መሆኑን ማረጋገጥ አለባት።

በዚህ ወቅት ሴቶች ምንም ነገር ወደ ብልታቸው ውስጥ እንዳያስገቡ ይመከራሉ። የወር አበባን ደም ለመምጠጥ በሴት ብልት ውስጥ የተገጠመ ለስላሳ ቁሳቁስም ቢሆን መጠቀም የለባቸውም። የመድኃኒት ፅንስ ማቋረጫ እንክብል ከተጠቀሙ በኋላ ከባድ የደም መፍሰስ እስኪቆም ድረስ ለ2 ቀናት ያህል በውሃ መዘፍዘፍ ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ የለባቸውም። ምክንያቱም የማህፀን ጫፍ ክፍት ሆኖ ስለሚቆይ ለበሽታ የመጋለጥ እድሏ ከፍተኛ ነው።

**አንዲት ሴት ፅንሱ ከተቋረጠ በኋላ ወዲያውኑ ማርገዝ ትችላለች!**
ወዲያውኑ ለማርገዝ ካልፈለገች እንዲሁም ያልተፈለገ እርግዝናን ለመከላከል ጥሩ እና አስተማማኝ የእርግዝና መከላከያ ዘዴን መጠቀም መጀመር ትችላለች።

## ORGANIZATIONAL INFORMATION

Women Help Women
WEB: HTTPS://WOMENHELP.ORG/
EMAIL: INFO@WOMENHELP.ORG
TWITTER: @WOMENHELPORG
FACEBOOK: WOMENHELPWOMENINTERNATIONAL

MAMA Network: Mobilizing Activists around Medical Abortion (MAMA).
WEB: WWW.MAMANETWORK.ORG



# ሚሶፕሮስቶል እንክብልን በመጠቀም የሚደረግ የሕክምና ፅንስ ማቋረጥ

## ሚሶፕሮስቶል ምንድን ነው?

ሚሶፕሮስቶል የመድሀኒት እንክብል እርግዝናን ለማቋረጥ እና የጨጓራ ቁስለትን ለማከም በመላው አለም ጥቅም ላይ የሚውል መድሃኒት ነው። በፋርማሲዎች ውስጥ በ “ሳይቶቴክ, አይዞቬንት, ሚሶክላር, ሚሶፌም, ሳይሩክስ ወይም ቶሚስፓል” ስም ይሸጣል። በአብዛኛዎቹ የአፍሪካ ሀገራት ይህ መድሀኒት የተመዘገበው እናቶች ልጅ ከወለዱ በኋላ የሚገጥማቸውን ከባድ የደም መፍሰስን ለማከም እና ለመከላከል በሚል ነው።

women help women

# ሚሶፕሮስቶል

## በምን ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል?

ከፅንስ መጨንገፍ ወይም ፅንስን ካቋረጡ በኋላ የሚወሰድ ሲሆን (ያላለቀ የፅንስ ማቋረጥን ለማጠናቀቅም ይጠቅማል)፡ ፡ እንዲሁም ከወሊድ በኋላ የሚከሰት ከባድ የደም መፍሰስን ለመከላከል እና ለማከም ይውላል፡፡

በተጨማሪም የጨጓራ ቁስለትን ለማከም ይረዳል።

## እንዴት ነው የሚሰራው?

ሚሶፕሮስቶል ማህፀን እንዲወጠር፣ እንዲለሰልስ እና የማህፀን በር እንዲከፈት ያደርጋል፤ ይህም ልክ እንደ የፅንስ መጨንገፍ ያለ ሂደትን ያስከትላል።

## ደህንነቱ የተጠበቀ ፅንስን ለማቋረጥ መቼ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል?

ከመጨረሻው የወር አበባ ዑደት የመጀመሪያው ቀን ጀምሮ በመቁጠር በእርግዝና የመጀመሪያዎቹ 12 ሳምንታት ውስጥ፡፡

## ደህንነቱ የተጠበቀ ፅንስን ለማቋረጥ ምን ሂደቶችን መከተል ያስፈልጋል?

አንዲት ሴት በአጠቃላይ 12 እንክብሎች ያስፈልጋታል እናም በየ 3 ሰዓቱ በ 3 ዶዝ ወይም ለ3 ጊዜ ያህል 4 እንክብል እንድትወስድ ይደረጋል። (3 ሰዓት)

የሚሶፕሮስቶል እንክብሎችን ከምላስ ስር ለ 30 ደቂቃ ያህል (30 ደቂቃ)

ማስቀመጥ ከዛም ሳይዋጥ በአፍ ውስጥ እንዲሟሟ ማቆየት/ ማድረግ

ከ 3 ሰአታት በኋላ ሌላ 4 እንክብሎችን ከምላስ ስር ለ 30 ደቂቃ ያህል (3 ሰዓት; 30 ደቂቃ)

ማስቀመጥ ከዛም ሳይዋጥ በአፍ ውስጥ እንዲሟሟ ማቆየት/ ማድረግ

ከ 3 ሰአታት በኋላ ሌላ 4 እንክብሎችን ከምላስ ስር ለ 30 ደቂቃ ያህል (3 ሰዓት; 30 ደቂቃ)

ማስቀመጥ ከዛም ሳይዋጥ በአፍ ውስጥ እንዲሟሟ ማቆየት/ ማድረግ

**ከ 3 ሰዓታት በኋላም ፅንስ ማቋረጡ ካልጀመረ/ ካልተከሰተ፣ ፅንሱ እስኪቋረጥ ድረስ በየ3 ሰዓት ልዩነት ተጨማሪ የእንክብል መጠን መጠቀም ይቻላል።**

## መድሃኒቱን ከተጠቀሙ በኋላ ምን ሊጠበቅ/ ሊከሰት ይችላል?

በወር አበባቸው ወቅት ከሚከሰተው በላይ ከፍተኛ ቁርጠት እና የሴት ብልት ደም መፍሰስ ይከሰታል፡፡

(24 ሰዓት) 80 በ100 በሚሆኑ ተመሳሳይ ክስተቶች መድሃኒቱ ከተወሰደ በመጀመሪያዎቹ 24 ሰዓታት ውስጥ ፅንሱ የመቋረጥ ሂደት ይጀምራል፡፡

የእርግዝና ጊዜዋ በረዘመ ቁጥር ከፍተኛ የደም መፍሰስ እና ቁርጠት ሊኖረው ይችላል።

**የህመም ማስታገሻ መድሃኒቶች ከመጀመሪያው የሚሶፕሮስቶል እንክብል ጋር በተመሳሳይ ጊዜ ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ ኢቡፕሮፌን የተሰኘው መድህኒት በጣም ውጤታማ ነው፡፡ በተጨማሪም ፓራሲታሞል / አሴታሚኖፌን መጠቀም ይቻላል፡፡**



## ሊከሰቱ የሚችሉ የጎንዮሽ ጉዳቶች

(24 ሰዓት) በመጀመሪያዎቹ 24 ሰዓታት ውስጥ የሚከተሉት ምልክቶች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ ማቅለሽለሽ፣ ማስታወክ፣ ተቅማጥ፣ ትኩሳት፣ ብርድ ብርድ የሚል ትኩሳት፣ ራስ ምታት ወይም ማዞር እና መፍዘዝ ናቸው፡፡ እነዚህ የጎንዮሽ ጉዳቶች አደገኛ የሚባሉ አይደሉም እንዲሁም በጥቂት ሰዓታት ውስጥ የሚጠፉ ናቸው፡፡

## የአደገኛ ወይም የማስጠንቀቂያ ምልክቶች (ውስብስብ ችግሮች) ምንድናቸው?

- ከመጠን በላይ ደም መፍሰስ (2 ወይም 3 የወር አበባ የንፅህና መጠበቂያ/ሞዴስ ለተከታታይ ለ2 ወይም 3 ሰዓታት በላይ መጠቀም)፡፡ (2 ሰዓት +)
- ከፍተኛ ትኩሳት (ከ 38 ወይም 39 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ) የሆነ የሰውነት ሙቀት ከ24 ሰአታት በላይ መቆየት፡፡ (39º; 24 ሰዓት +)
- መድሃኒቱን ከወሰዱ ከጥቂት ቀናት በኋላ በህመም ማስታገሻዎች የማይጠፉ ከፍተኛ ህመም መሰማት፡፡
- ያልተለመደ እና ሽታ ያለው፣ የሴት ብልት ፈሳሽ መኖር።

## አደገኛ ወይም ውስብስብ ችግሮቹ ሲኖሩ ምን ማድረግ ይጠበቅብዎታል?

**ወዲያውኑ ወደ ጤና ጣቢያ ይሂዱ፡፡**

የሕክምና ድንገተኛ አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ የሕክምና ባለሙያዎች ግለሰቧን በጊዜው የመርዳት ግዴታ አለባቸው፡፡ በሕክምና ፅንስን ካቋረጡ በኋላ የሚኖረው ውስብስብ ችግሮች በፅንስ መጨንገፍ ከሚመጡ ችግሮች ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ በተፈጥሮ ፅንስ መጨንገፍ እና በሚሶፕሮስቶል ፅንስ ማቋረጥ መካከል ያለውን ልዩነት መለየት አይቻልም። በመሆኑም የሕክምና እንክብካቤ የሚያስፈልጋት ሴት ለህክምና ባለሙያዎቹ የፅንስ መጨንገፍ እንደጀመራት ልትናገር ትችላለች፡፡